የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ-ሐምሌ ፴ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 58
ADDIS ABABA- 6th August, 2005

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

የትራንስፖርት አዋጅ...ገጽ ፫ሺ፩፻፹፩

CONTENTS

Proclamation No. 468/2005

Transport Proclamation ........ Page 3181

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯

## ትራንስፖርትን ስለመቆጣጠር የወጣ አ ዋ ጅ

ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ዕድገት የትራንስፖርት አገልግሎት የበለጠ ተወዳዳሪ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ብቃት ያለው ሆኖ እንዲራመድ ክትትል ስለሚያስፈልገው፤

የትራንስፖርት አደረጃጀት የመንግሥት ፖሊሲን በአግባቡ ለመተግበር አመቺ ሁኔታ በሚፈጥር መልኩ እንደገና መዋቀር ስለሚገባው፤

ትራንስፖርትን አስመልክቶ የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር በማያሻማ ሁኔታ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ «የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

## PROCLAMATION NO. 468/2005.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE REGULATION OF TRANSPRT

**WHEREAS,** the economic and social development of the country requires that transport service be regulated to make it more competitive, safe and efficient;

**WHEREAS,** the transport sector has to be restructured in a manner to create favorable conditions for the smooth and effective implementation of the government transport policy;

**WHEREAS,** it has become necessary to clearly define the powers and duties of the executive organs at the federal and state levels with regard to transport;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Transport Proclamation No. 468/2005."

**2. Definitions**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

ያንዱ ዋጋ 5·15
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩/ «ሚኒስቴር» ወይም «ሚኒስትር» ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፪/ «ማህበር» ማለት የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የተቋቋመና በዚህ አዋጅ መሰረት የተመዘገበ ማህበር ነው፤

፫/ «የንግድ የመንገድ ማመላለሻ» ማለት በግለሰብ ወይም በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል በሚካሄድ ድርጅት መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን ለኪራይ፣ ለጥቅም ወይም ለትርፍ የማመላለስ ሥራ ሆኖ እንደሚከተለው የግል ወይም የህዝብ ተብሎ ይከፈላል፤

ሀ) «የግል የንግድ የመንገድ ማመላለሻ» ማለት መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን የሚያመላል ሰው ተሽከርካሪ ንብረትነቱ የድርጅቱ ሆኖ፤

(i) የሚመላለሱት ዕቃዎች የዚያው የድርጅት ንብረት የሆኑ ወይም ለጥገና ወይም ለማደስ በአደራ የተሰጡት የሆኑ እንደሆኑና ዕቃዎቹን ማመላለስ ለድርጅቱ ዓይነተኛ የንግድ ሥራ አስፈላጊና ማሟያ የሆነ እንደሆነ፣ ወይም

(ii) የሚመላለሱት መንገደኞች የዚያው ድርጅት ሠራተኞች ሆነው የሚመላለሱትም ወደ ሥራ ቦታቸውና ከሥራ ቦታቸው የሆነ ወይም የድርጅቱን ሥራ ለማከናወን የሆነ እንደሆነ ነው፤

ለ) «የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ» ማለት የግል ተብሎ ያልተመደበ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሁሉ ነው፤

፬/ «የዲሲፕሊን መምሪያ» ማለት በሚኒስትሩ የወጣ የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰንና አፈጻጸም መምሪያ ነው፤

፭/ «አውራ ጎዳና» ማለት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የሚያስተዳድረውና አውራ ጎዳና ብሎ የሚሰይመው መንገድ ነው፤

፮/ «የስምሪት ፕሮግራም» ማለት የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን የዓመት፣ የወር፣ የሣምንት ወይም የቀን እንቅስቃሴ የሚወስን ድልድል ነው፤

፯/ «የስምሪት መስመር» ማለት በባለሥልጣኑ የሚወሰን የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የስምሪት መነሻና መድረሻ ነው፤



1/ "Minster" or "Ministry" means the Minister or Ministry of Infrastructure, respectively;

2/ "Association" means an association established by persons and enterprises engaged in public commercial road transportation and registered in accordance with this Proclamation;

3/ "Commercial Road Transport" means the carrying by a natural or juridical person, or passengers or goods for hire, remuneration or profit, classified as either private or public as follows:

a) "Private Commercial Road Transport" means if the vehicle used for carrying passengers or goods is owned by the enterprise, and

(i) in the case of goods being transported, the goods are owned by the enterprise or have been entrusted to it for the purpose of repairs or transportation by it and the transportation of said goods is necessary and complementary to the principal commercial activity carried out by the enterprise; or

(ii) in the case of passengers being transported, the passengers are employees of the enterprise and are being transported to or from their place of work or are engaged in the business of the enterprise;

b) "Public Commercial Road Transport" means all commercial road transport not classified as private;

4/ "Disciplinary Directives" means directives issued by the Minister in accordance with which disciplinary measures to be taken, decided and enforced;

5/ "Highway" means a road administered and designated as such by the Ethiopian Roads Authority;

6/ "Trip Schedule" means yearly, monthly, weekly or daily program fixed for the movement of public commercial road transport vehicles;

7/ "Route of Operation" means a place of departure and destination to be determined by the Authority where public commercial road transport vehicles are assigned to operate.

፰/ «የመንጃ ፍቃድ» ማለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ለመንዳት የሚያስችል በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚሰጥ የመንጃ ፈቃድ ነው፤

፱/ «የፌዴራል የመንጃ ፈቃድ» ማለት በጋራ ጥቅም መርሕ /ሪስፕሮሲቲ/ መሠረት ለውጭ አገር ዜጎች ወይም ለጉብኝት፣ ለንግድ ሥራ ወይም ለመንግሥት ሥራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ባለሞተር ተሽከርካሪ ለማሽከርከር የሚያስችል በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚሰጥ የመንጃ ፈቃድ ነው፤

፲/ «መንገደኛ» ማለት በተሽከርካሪ ተሣፍሮ የሚሄድ ማንኛውም ሰው ሲሆን ነጂውን፣ ገንዘብ ተቀባዩንና በተሽከርካሪው ላይ የተመደበ ማንኛውንም ሌላ ሠራተኛ አይጨምርም፤

፲፩/ «ክትትል» ማለት የትራንስፖርት አዋጅ፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎችና ውሳኔዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ተግባር ነው፤

፲፪/ «መንገድ» ማለት ለማናቸውም ተላላፊ ክፍት ካል ሆነ የግል መንገድ በስተቀር ተሽከርካሪዎች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ማናቸውም ጎዳና፣ የከተማ መንገድ፣ አውራ ጎዳና ወይም መተላለፊያ ነው፤

፲፫/ «ተሽከርካሪ» ማለት ልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን ሳይጨምር በመንገድ ላይ በመንኮራኩር የሚሄድ ማንኛውም ዓይነት ተሽከርካሪ ሆኖ ሠረገላ፣ ብስክሌት፣ ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ግማሽ ተሣቢ እና ተሣቢ ተብሎ ይከፈላል፤

፲፬/ «ሠረገላ» ማለት ከብስክሌት፣ ከባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ከግማሽ ተሣቢ እና ከተሣቢ በስተቀር ማናቸውም ተሽከርካሪ ነው፤

፲፭/ «ብስክሌት» ማለት በሚነዳው ሰው ኃይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ነው፤

፲፮/ «ባለሞተር ተሽከርካሪ» ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሣቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ሆኖ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ባለሞተር ብስክሌት፣ የግል አውቶሞቢል፣ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ጎታች መኪና እና ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ ተብሎ ይከፈላል፤

፲፯/ «የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ» ማለት ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራና ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን ጎታች መኪናን ይጨምራል፤

8/ "Driving License" means a permit to drive a motor vehicle issued in accordance with regulations and directives issued under this Proclamation;

9/ "Federal Driving License" means a permit to drive a motor vehicle issued to foreigners based on the principle of reciprocity or to Ethiopians going abroad for tour, business or official duties in accordance with regulations and directives issued under this Proclamation;

10/ "Passenger" means any person riding in a vehicle, other than the driver, cashier or any other person assigned to work on a vehicle;

11/ "Follow-up" means the ascertainment of the proper implementation of road transport laws, regulations, directives, standards and decisions;

12/ "Road" means any road, street, highway or any other travel route, customarily used by vehicles other than private roads not open to all traffic;

13/ "Vehicle" means any type of wheeled vehicle, other than special military vehicles, for use on roads classified as carriage, bicycle, motor vehicle, semi-trailer and trailer;

14/ "Carriage" means any vehicle other than a bicycle, a motor vehicle, a semi-trailer and a trailer;

15/ "Bicycle" means a vehicle moving by the motive power of the person operating the same;

16/ "Motor Vehicle" means a vehicle moving by mechanical or electrical power, classified as truck, motorcycle, private motor car, public service vehicle, truck tractor and special mobile equipment;

17/ "Truck" means a motor vehicle constructed or adapted for use and used primarily for the conveyance of goods of any description and includes a truck tractor;

፲፰/ «ባለሞተር ብስክሌት» ማለት የጎን ተሽከርካሪውን ሳይጨምር ክብደቱ ከ፬፻ ኪሎ ግራም የማይበልጥ ከአራት መንኰራኩር በታች ያለው ባለሞተር ተሽከርካራ ነው፤

፲፱/ «የግል ተሽከርካሪ» ማለት ከጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ከባለሞተር ብስክሌት፣ ከሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ከጎታች መኪና እና ከልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ የተለየ ለግል መጠቀሚያ የሚውል ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

፳/ «የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ» ማለት መንገደኞችን ለማመላለስ የሚያገለግል ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን የንግድ አውቶሞቢልና አውቶቡስ ተብሎ ይከፈላል፤

፳፩/ «የንግድ አውቶሞቢል» ማለት ከአሥራ ሁለት የማይበልጡ መንገደኞችን የሚያሳፍር የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው፤

፳፪/ «አውቶቡስ» ማለት ከአሥራ ሁለት መንገደኞች በላይ ለማሳፈር የሚችል የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው፤

፳፫/ «ጎታች መኪና» ማለት በተለይ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ለመጎተት የሚያገለግል ሆኖ የሌላ ጭነትን ሳይሆን የሚጎትተውን ተሽከርካሪና በርሱ ላይ ያለውን ጭነት ክብደት ብቻ በከፊል ለመሸከም የተሰራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

፳፬/ «ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ» ማለት ሰውን ወይም ዕቃን በመንገድ ላይ እንዲያመላልስ ሆኖ የተሰራ ተሽከርካሪ ሳይሆን ለእርሻ፣ ለአትክልት፣ ለከብት እርባታ፣ ለመንገድ፣ ለሕንፃ፣ ለቁፋሮ ወይም ለማናቸውም ተመሳሳይ ሌላ ሥራ የተሰራ ወይም ለዚሁ ጉዳይ እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

፳፭/ «ግማሽ ተሳቢ» ማለት ለመንገደኞች ወይም ለጭነት ማመላለሻ የሚያገለግልና በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚሳብ ሆኖ የተሽከርካሪውም ጭነቱም ክብደት በከፊል በሌላ ተሽከርካሪ ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ እንዲሳብ ተደርጎ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፤

፳፮/ «ተሳቢ» ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ኃይል የሌለው ሆኖ ጎታች በሆነ በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ሊቀጠልና ሊጎተት የሚችልና ክብደቱ ጎታች በሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ እንደማያርፍ ሆኖ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፤ ሆኖም ከባለሞተር ብስክሌት ጋር ተያይዞ የሚሳበውን የጎን ተሽከርካሪ አይጨምርም፤

18/ "Motorcycle" means a motor vehicle with less than four (4) wheels, the weight of which, exclusive of any side-car attached thereto, does not, when unladen exceed four hundred kilograms;

19/ "Private Vehicle" means a motor vehicle used for private service other that a truck, a motorcycle, a public service vehicle, a truck tractor and special mobile equipment;

20/ "Public Service Vehicle" means a motor vehicle used to carry passengers and classified as commercial motor car and motor omnibus;

21/ "Commercial Motor Car" means a public service vehicle having accommodation for not more than twelve passengers;

22/ "Motor Omnibus" means a public service vehicle having accommodation for more than twelve passengers;

23/ "Truck Tractor" means a motor vehicle constructed or adapted for use and used primarily for drawing other vehicles, and so constructed as to carry no load other than a part of the weight of the vehicle and load being drawn;

24/ "Special Mobile Equipment" means any vehicle designed, adapted or used for agricultural, horticultural, livestock raising, road construction, building, digging or any other similar operation; this term does not include vehicles designed or used for the transportation of persons or goods;

25/ "Semi-trailer" means a vehicle constructed or adapted for use and used for use and used for carrying persons or goods and being drawn by a motor vehicle, and so constructed that some part of its weight and that of its load rests upon or is carried by another vehicle;

26/ "Trailer" means a vehicle which has no independent motive power and which is capable of being attached to and drawn by a motor vehicle, and so constructed that no part of its weight rests upon the motor vehicle by which it is drawn, but shall not include a side car attached to a motorcycle;

፳፯/ «ክልል» ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ያካትታል፤

፳፰/ «አገር አቋራጭ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት» ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን በሚያገናኝ መንገድ ላይ የሚካሄድ ማናቸውም የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ነው፤

፳፱/ «ዓለም አቀፍ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት» ማለት የኢትዮጵያ ድንበሮችን አቋርጦ የሚካሄድ ማንኛውም የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ወይም እንቅስቃሴ ነው፤

፴/ «ትራንስፖርት» ማለት በመንገድ፣ በሀዲድና በውሃ ላይ በሞተር ኃይል በሚንቀሳቀሱ አጓጓዦች የሚደረግ የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፤

፴፩/ «መርከብ» ማለት በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ የውሃ ማጓጓዣ ነው፤

፴፪/ «ቢሮ» ማለት የትራንስፖርት ሕጎችን የሚያስፈጽም የክልል አስፈጻሚ አካል ነው፤

፴፫/ «የምድር ባቡር» ማለት በምድር ባቡር ሐዲድ ላይ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው፤

፴፬/ «ሐዲድ» ማለት ለባቡር መሄጃ ተብሎ የተሰራ መተላለፊያ ነው፤

፴፭/ «ባሕረኛ» ማለት በኢትዮጵያ መርከብ ወይም በአገር አቋራጭ የውሃ ላይ ማጓጓዣ ላይ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ እንዲሰራ የተደረገ ማንኛውም ሰው ሲሆን አዛዡን፣ ነጅውንና ለማጁን ያጠቃልላል::

## ፫. <u>የአፈጻጸም ወሰን</u>

ለክልል ቢሮዎች በሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ፣

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ መንገዶች አጠቃቀም፣ በመንገዶች በሚገለገሉ ተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች፣

፪/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ሐዲዶች አጠቃቀም፣ በሐዲዶች በሚገለገሉ ባቡሮችና ነጂዎች፣ እና

፫/ በኢትዮጵያ መርከቦችና ባህረኞች፣

እንዲሁም በጠቅላላ የየብስና የውሃ ትራንስፖርት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

27/ “State” means a state specified in Article 47 of the Constitution and includes the Addis Ababa and Diredawa City Administrations;

28/ “Cross-country Road Transport Service” means any commercial road transport service conducted on roads linking two or more than two States;

29/ “International Road Transport Service” means any road transport service or movement conducted on the roads across the boundaries of Ethiopia;

30/ “Transport” means any transport service undertaken on road, railway and water by motor power carriers;

31/ “Ship” means a seaplane carrier moving by engine power;

32/ “Bureau” means a State executive organ in charge of enforcing transport laws;

33/ “Train” means any vehicle moving on the rails of a railway lines;

34/ “Rail” means any travel route used by train;

35/ “Seafarer” means any person including master, pilot and apprentice employed or assigned on board on Ethiopian ship or any cross country water transport vessel.

## 3. Scope of Application

Without prejudice to the powers and duties given by law to State Bureaux, this, Proclamation shall apply:

1/ to the use of any road within Ethiopia, vehicle using the roads and their drivers;

2/ to the use of any railways within Ethiopia, trains using the railways and their operators;

3/ to Ethiopian ships and seafarers;

As well as to all matters related to land and water transport.

## ክፍል ሁለት
## የትራንስፖርት ባለሥልጣን

### ፬. መቋቋም

፩/ የትራንስፖርት ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ «ባለሥልጣን» እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

፪/ ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል::

### ፭. ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ውስጥ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊያቋቁም ይችላል::

### ፮. የባለሥልጣኑ ዓላማዎች

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

፩/ ቀልጣፋ፣ ብቁ፣ ኤኮኖሚያዊ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት ሲስተም እንዲስፋፋ ማድረግ፤

፪/ የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀና ምቾት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤

፫/ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት መሥመሮች እንዲዘረጉና እንዲደራጁ ማድረግ፤ እና

፬/ ትራንስፖርት በማንኛውም ረገድ እንዲያድግ ማበረታታት::

### ፯. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ ትራንስፖርትን በአጠቃላይ በተመለከተ፤

ሀ) ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሳቦችን አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፣ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤

ለ) ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ የተሟላና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት መኖሩን መከታተል፤

ሐ) ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የመንግስት ፖሊሲዎችና ሕጎችን እንዲሁም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሥራ ላይ ማዋልና ማስፈጸም፤

## PART TWO
## TRANSPORT AUTHORITY

### 4. Establishment

1/ The Transport Authority (hereinafter the "Authority") is hereby established as an autonomous public authority having separate juridical personality.

2/ The Authority shall be accountable to the Ministry.

### 5. Head Office

The Authority shall have its head office in Addis Ababa and may establish branch offices at any other place, as may be necessary.

### 6. Objectives of the Authority

The Authority shall have the following objectives:

1/ to promote an efficient, adequate, economical and equitable transport system;

2/ to ensure that public transport services are safe and comfortable;

3/ to develop domestic and international transport network; and

4/ to promote the development of all aspects of transport.

### 7. Powers and Duties of the Authority

The Authority shall have the powers and duties to:

1/ with respect to transport in general:

a) prepare and submit policy proposals to the Ministry relating to transport and implement same upon approval;

b) follow up the provision of safe, efficient, adequate and equitable transport services to the public;

c) implement and enforce government policies and laws relating to transport as well as treaties to which Ethiopia is a party;

መ) በአገር ደረጃና ዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት መስመሮች እንዲዘረጉ ማድረግ፤

ሠ) የተቀናጀ የሕዝብና የዕቃ ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲስፋፋ ማድረግ፤

ረ) መንገደኞች፣ ዕቃዎችና ፖስታዎች በንግድ ትራንስፖርት ስለሚጓዙበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና አፈፃፀሙን መከታተል፤

ሰ) ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎችንና ስታትስቲኮችን በቋሚ ሁኔታ መሰብሰብና ማጠናቀር፤

ሸ) ስለትራንስፖርት አገልግሎት እንደ አግባቡ የሥልጠናና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ እንደአስፈላጊነቱም የማሰልጠኛ ተቋሞችን ማቋቋምና ማካሄድ፤

ቀ) ትራንስፖርት በማናቸውም ረገድ ስለሚያድግበት ሁኔታ ጥናቶችን ማካሄድ፣ እንዲካሄድ ማበረታታት እንዲሁም ፕላንና ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

በ) ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የአካባቢ መበከልን ለመከላከል ከተሽከርካሪዎችና ባቡሮች ስለሚወጣው ጪስ፣ ጋዝ፣ ተንና ስለመሳሰሉት ከአገሪቱ አቅምና ከዓለም አቀፍ መመዘኛዎች ጋር የተገናዘበ ደረጃ አዘጋጅቶ ማቅረብ፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን መከታተል፤

ተ) ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ማስወሰንና መሰብሰብ፤

ቸ) በህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ በተሰማሩት ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ማህበራት የገበያ እጦት ሲያጋጥም ወይም በተገልጋይ ህብረተሰብ የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት ሲከሰት ክትትል ማድረግ፤ እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትና ፍላጎት መጣጣሙን ማረጋገጥና ስምሪቱ ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ፤

ኀ) የቢሮዎችን አቅም ለማጎልበት አመች ሁኔታዎችን ማመቻቸት::

፪/ የመንገድ ትራንስፖርትን በተመለከተ፤

ሀ) በመንገዶች የሚጠቀሙ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ከሚሰጡት አገልግሎት ዓይነት ሊኖራቸው የሚገባውን የደህንነት መሳሪያዎች ክብደትና መጠናቸውን እንዲሁም የተሳፋሪን ብዛትና የጭነት ክብደት መወሰን፤ በዚሁም መሠረት ምዝገባ እንዲካሄድ የማረጋገጫ ሰርትፊኬት መስጠት፤



d) cause the development of domestic and international transport service network;

e) develop an integrated system of transport for passengers and goods;

f) issue and follow up the implementation of directives relating to conditions under which passengers, goods and mail may be transported by commercial transport;

g) collect and compile, on regular basis, any information and statistical data relating to transport;

h) render, as may be appropriate, training and consultancy services relating to transport service; establish and operate training institutions as may be necessary;

i) undertake studies and prepare plans and programs to promote the development of all aspects of transport,encourage studies to be conducted and implement same upon approval;

j) in cooperation with the concerned organ prepare and submit and, upon approval, implement standards relating to the smoke, gas, vapour and the like emitted from the exhaust pipes of vehicles and trains with a view to preventing pollution taking into account international criteria and the capacity of the country;

k) submit for approval and collect fees for services rendered;

l) follow up that persons and individuals engaged in public commercial road tansport in case of market failure or the public faces transport shortage and ensure the compliance of transport service supply and demand at national level as well as make the trip equitable;

m) facilitate the capacity of the Bureaus.

2/ with respect to road transport:

a) determine the operations, equipment, weight, size, number of passengers and load of vehicles using the road and issue approval certificate for registration accordingly;

ለ) በአገር አቋራጭና ዓለም አቀፍ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የሙያ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠትና መከታተል፤

ሐ) ከውጭ ሀገር የሚመጡትንና በአገር ውስጥም የሚሰሩትን፣ የሚገጣጠሙትን ወይም በከፊል የሚሰሩትን ማናቸውንም ባለሞተር ተሽከርካሪዎች መከታተል፤ ለዚሁም መመዘኛ (ስፔሲፊኬሽን) ማውጣት፤

መ) በአገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ወይም ንብረትነታቸው የዲፕሎማቲክ፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከአንድ ክልል በላይ የሚንቀሳቀሱ የተራድኦ ድርጅቶች ወይም የፌዴራል መንግሥት የሆኑ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን መመዝገብና የቴክኒክ ምርመራ ማካሄድ እንዲሁም መከታተል፤

ሠ) መንጃ ፈቃድን የሚመለከት መመሪያ ማውጣትና ተግባራዊነቱን መከታተል፤ የፌዴራል የመንጃ ፈቃድ መስጠትና ማደስ፤

ረ) በባለሥልጣኑ ወይም በክልል ቢሮዎች በሚመዘገቡ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፉ ሠሌዳዎች ማምረት፤

ሰ) በአገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የህዝብ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩት ሰዎች፣ ድርጅቶች ወይም ማህበራት የሚያስከፍሉትን ታሪፍ ለሚሰጡት አገልግሎት ማግኘት ስለሚገባቸው ጥቅምና የተጠቃሚውን የመክፈል አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ማጽደቅ፤

ሸ) በዓለም አቀፍ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ወይም በተመሳሳይነት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች የትራንዚት ፈቃድ መስጠትና መከታተል፤

ቀ) ስለተሽከርካሪዎች አመዘጋገብና የቴክኒክ ምርመራ መመሪያ ማውጣትና መከታተል፤

በ) ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት ለሚያስተምሩ ሰዎችና ትምህርት ቤቶች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ማውጣትና ተግባራዊነቱን መከታተል፤

ተ) ማናቸውንም የተሽከርካሪ መጠገኛና ማደሻ ጋራዥ የቴክኒክ ብቃት ስለማረጋገጥ፣ የሥራ ፈቃድ አሰጣጥና ስለደረጃው አወሳሰን መመሪያ ማውጣትና ተግባራዊነቱን መከታተል፤

b) issue certificate of competence to, and follow up persons and enterprises engaged in cross-country and international commercial road transport;

c) follow up the importation, manufacture or assembling of vehicles in Ethiopia and for this purpose issue technical specifications;

d) conduct annual registration and technical inspection to motor vehicles, engaged in cross-country and international commercial road transport service or which are owned by diplomatic missions, international organizations, aid organization operating in more than one State or the Federal Government, and follow up same;

e) issue and follow up the implementation of directives relating to driving license; issue and renew federal driving license;

f) manufacture plates to be affixed on those vehicles to be registered by the Authority or State Bureaux;

g) approve tariff proposed by persons, organizations or associations engaged in cross-country and international passenger transport, taking into account their benefit they should get from the service provided and the capacity of the users to pay;

h) issue a transit permit to vehicles and their drivers engaged in international commercial road transport or other related services and follow up same;

i) issue directives for registration and inspection of vehicles and follow up same;

j) issue and follow up the implementation of directives relating to the licensing of driving schools and instructors;

k) issue and supervise the implementation of directives relating to the certification of the technical competence, licensing and grading of garages engaged in the repair and maintenance of vehicle;

ቸ) ለሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መናኸሪያዎች ደረጃና መመዘኛ (ስፔስፍኬሽን) ማውጣትና መከታተል፣

ኀ) በአገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የሕዝብ ማመላለሻ ሥራ ለሚሰማሩ ተሽከርካሪዎች ማኅበራት የሚያቀርቡለትን የስምሪት ፕሮግራም ማጽደቅ፣ ካልቀረበለትም ራሱ ማዘጋጀትና ለዚሁ የወጣውን የዲሲፕሊን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በገበያ ሥርዓት አገልግሎት እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

ነ) የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ወይም የማህበራዊ ችግሮች ሲከሰቱ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ሚኒስቴሩ በሚያፀድቀው መመሪያ መሠረት በአስፈላጊው ቦታና መስመር ደልድሎ ማሰራትና መከታተል፣

ኘ) በአገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለስ ሥራ ላይ የተሰማሩት ሰዎችና ድርጅቶች የሚያቋቁሙአቸውን ማህበራት መመዝገብ፣ ስለ አሠራራቸው መመሪያ ማውጣትና መከታተል፣

አ) ባለሞተር ተሽከርካሪዎች በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሱት አደጋ የመድን ዋስትና ሽፋን እንደሚኖራቸው ማረጋገጥ፣ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ለሚጓጓዙ መንገደኞችና ዕቃዎች ሊኖር ስለሚገባው የመድን ዋስትና ሽፋን መመሪያ ማውጣትና ማስፈፀም፣

ከ) ተሽከርካሪዎች እንደገና ስለሚሰሩበት፣ ስለሚፈታቱበት ወይም ከጥቅም ውጭ ስለሚደረጉበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና መከታተል፣

ኸ) በአውራ ጎዳናዎች ላይ የመንገድ ትራንስፖርት አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን መከታተል፣

ወ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአገር አቋራጭ እና በዓለም አቀፍ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ተሽከርካሪዎችን የቀለም ዓይነትና ዓርማ መወሰን፣

ዐ) በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች፣ ማኅበራት፣ የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ተጠቃሚዎች የሚወከሉበት አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋም፣

l) issue standards and specification of terminals that serve for public commercial road transport vehicles and follow up same;

m) approve trip schedules prepared by associations for vehicles engages in cross-country and international public road transport service and when the schedule is not made available prepare same and enforce disciplinary directives issued thereon and facilitate free market service as maybe nessary;

n) in case of natural disasters or temporary economic or social crisis, mobilize commercial road transport vehicles to operate in areas and routes where their service are demanded in accordance with directives given by the Ministry and follow up same;

o) register associations established by persons and organizations engaged in cross-country and international public commercial road transport; issue directives and supervise their activities;

p) ensure that all motor vehicles have third party insurance coverage; and in consultation with the appropriate organs, issue and enforce directives relating to the provision of insurance policy coverage for passengers and cargo;

q) issue directives regarding the refurbish, scraping or destroying of motor vehicles and follow up same;

r) follow up the enforcement of road transport Proclamations, regulations and directives on highways;

s) determine, where necessary, the color and distinguishing makes of commercial road transport vehicles engaged in cross-country and international road transport;

t) form an advisory committee comprising members representing persons, enterprises and associations engaged in public commercial road transport, the concerned government organs and users;

ዘ) የተሽከርካሪ ዋጋ ግምት የመተመን አገልግሎት መስጠት፤

ዠ) የመካከለኛ የትራንስፖርት መገልገያ መሣሪያ ዎች በአገሪቷ የቦታ አቀማመጥ በሚያመች መልኩ እንዲስፋፋ ማበረታታት::

፫/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ድንጋጌ ቢኖርም ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ የሆኑ ከተሞችን የመንገድ ትራንስፖርት በተመለከተ፤

ሀ) የትራንስፖርት አገልግሎቱ እንዲስፋፋ ማድረግ፤ የአውቶቡስና የታክሲ ፌርማታዎች፣ መናኸሪያዎችና መድረሻዎች እንዲሰሩ ማድረገና ማስተዳደር፤

ለ) ተሽከርካሪዎችን መመዝገብ፤ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ማካሄድና መከታተል፤

ሐ) በትራንስፖርት ሥራ የተሰማሩ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ማደራጀት፤ የትራፊክ አመራር ውጤታማ የሚሆንበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ፤ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፤

መ) በትራንስፖርትና በጋራዥ አገልግሎት ለሚሰ ማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፤

ሠ) ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት ለሚያስተምሩ ሰዎችና ትምህርት ቤቶች የሥራ ፈቃድ መስጠት፤ የመንጃ ፈቃድ መስጠት፤

ረ) የሕዝብን ደኅንነት የሚጎዱ ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በመከታተል ማገድ፤

ሰ) ከከተሞቹ ትራንስፖርት አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፤

፬/ የምድር ባቡር ትራንስፖርትን በተመለከተ፤

ሀ) ለባቡር ነጂዎች ፈቃድ መስጠትና ማደስ፤

ለ) ባቡሮችን መመዝገብና የቴክኒክ ምርመራ ማካሄድ፤

ሐ) ስለምድር ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ማውጣት፤

መ) በኢትዮጵያ ውስጥ መንገደኞችና ዕቃዎች በምድር ባቡር ስለሚጓጓዙበት ሁኔታ ደረጃ ማውጣትና መከታተል፤

u) provide vehicle valuation service.

v) Encourage the expansion of intermediate transport machinery in compliance with landscape of the country.

3/ notwithstanding the provisions of Article 3 of this Proclamation, with respect to road transport in cities accountable to the Federal Government:

a) promote the expansion of the transport service; cause the construction and administer bus and taxi stops and terminals;

b) register vehicles, undertake annual technical inspection and follow up;

c) organize individuals and enterprises engaged in transport services; design and implement mechanisms on the effectiveness of traffic management; provide capacity building support;

d) issue certificate of competence to individuals and enterprises engaged in transport and garage services;

e) issue license to driving lesson institutions and trainers; issue driving license;

f) follow up and suspend the operation of vehicles that could affect the safety of the public;

g) carry out other activities related to the cities' transport services;

4/ with respect to railway transport:

a) issue and renew license to train operators;

b) register trains and carry out technical inspection thereon;

c) issue directives regarding railway transport services;

d) issue standards and follow up under which passengers and goods may be transported by train;

ሠ) የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶችን መመዝገብ፣ የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠትና መከታተል፤

ረ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የባቡር አደጋ ሲከሰት መመርመርና ሪፖርት ማቅረብ፤

ሰ) የባቡሮችን አሰራር፣ ሊኖራቸው የሚገባውን መሳሪያዎች ክብደትና መጠናቸውን እንዲሁም የተሳፋሪን ብዛትና የጭነት ክብደት መወሰን፤

ሸ) ለባቡር መጠገኛ ጋራዥ የብቃት ሠርተፍኬት መስጠት፤

ቀ) የባቡር ቴርሚናሎችን ደረጃ ማውጣት፤

በ) የሐዲድ መስመሮችና የዲዛይን ደረጃ ማውጣት፤

ተ) የሐዲድ መስመሮችና የደህንነት መሣሪያዎች የወጣላቸውን መስፈርት ማሟላታቸውን ማረጋገጥ፤

፭/ የውሃ ትራንስፖርትን በተመለከተ፤

ሀ) በብሔራዊና ዓለም አቀፍ ሕጐች መሠረት፣

(i) የኢትዮጵያ መርከቦችንና አገር አቋራጭ የውሃ ላይ መጓጓዣዎችን መመዝገብና የባህር ጉዞ ብዙነት የምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ፤

(ii) ለባህረኛ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትና የባህረኛ ደብተር መስጠትና ማደስ፤

(iii) በኢትዮጵያ መርከቦችና በአገር አቋራጭ የውሃ ላይ መጓጓዣዎች እንዲሁም በመሣሪያዎቻቸው ላይ አስፈላጊውን የቴክኒክ ምርመራ እንዲካሔድ ማድረግ፤

ለ) የባህር ማመላለሻ አደጋ በደረሰ ጊዜ የፍለጋና የማዳን ተግባር እንዲካሔድ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤

ሐ) የባህረኞች ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲቋቋሙ ማበርታታትና በአገሪቷና በዓለም አቀፍ ሕጎች መሠረት ደረጃቸውን መወሰን፤

፮/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ መክሰስና መከሰስ፤ እና

e) register persons and organizations engaged in railway transport service, issue certificate of professional competence and follow up same;

f) in cooperation with the concerned bodies investigate and submit report in case of train accident;

g) determine the operation, equipment, weight, size, number of passengers and load of train using the railway;

h) issue certificate of competence to train repairing warehouses;

i) set standards of railway terminals;

j) determine design standard for railway lines;

k) ensure that railway lines and railway equipments comply with the safety standards set thereof;

5/ with respect to marine transport:

a) in accordance with domestic and international laws:

i) register Ethiopian ships and cross country water transport vessels and issue certificate of sea worthiness and renew same;

ii) issue and renew certificate of competence and seaman's book to seafarers;

iii) cause the necessary technical inspection to be undertaken on Ethiopian ships and their equipment;

b) cause search and rescue operation measures to be undertaken in case of marine accident;

c) encourage the establishment of marine training institutes and set their standards in accordance with domestic and international laws.

6/ own property, enter into contracts, sue and be sued; and

፯/ ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ ተግባሮችን ማከናወን::

፰. የባለሥልጣኑ አመራር

ባለሥልጣኑ፣

፩/ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ እና

፪/ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፣
ይኖሩታል::

፱. የዋና ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋናው ሥራ አስኪያጅ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋናው ሥራ አስኪያጅ፣

ሀ) በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ) የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸምና የሒሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል::

፫/ ዋናው ሥራ አስኪያጅ ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም እርሱን ተክቶ የሚሠራው ኃላፊ ከ፴ ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የሚሠራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለሚኒስትሩ ቀርቦ መጽደቅ አለበት::

7/ perform other lawful activities necessary for the carrying out of its duties and responsibilities.

**8. Management of the Authority**

The Authority shall have:

1/ a General Manager to be appointed by the Government upon the recommendation of the Minister; and

2/ the necessary staff.

**9. Powers and Duties of the General Manager**

1/ The General Manager shall, subject to the general directives of the Ministry, direct and administer the activities of the Authority.

2/ Without limiting the generality of the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the General Manager shall:

a) exercise the powers and duties vested in the Authority under this Proclamation;

b) employ and administer the employees of the Authority in accordance with the federal civil servants laws;

c) prepare and submit to the Ministry the work program and budget of the Aruthority; and implement same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Authority;

e) represent the Authority in all its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry annul operational and financial reports of the Authority.

3/ The General Manager may delegate part of his powers and duties to the officials and other employees of the Authority to the extent necessary for the efficient management of the activities of the Authrotiy; provided, however, that the prior consent of the Minister is required where such official is to act on behalf of the General Manager for more than 30 days.

## ፲. በጀት

የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፤

፩/ ባለሥልጣኑ ለሚሰጠው ፈቃድና አገልግሎት ከሚያስከፍለው ክፍያ፤

፪/ በመንግሥት ከሚሰጥ የበጀት ድጋፍ፤ እና

፫/ ከማናቸውም ሌላ ምንጭ::

## ፲፩. ስለሂሣብ መዛግብት

፩/ ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል::

፪/ የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ::

## ክፍል ሦስት

## የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ስለማካሄድና ስለ ሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማኅበራት

## ፲፪. የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ስለማካሄድ

፩/ ማንኛውም ግለሰብ ወይም በሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ሊሠማራ ይችላል::

፪/ በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለመሠማራት ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎችና ድርጅቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ መሠረት የሚቋቋም ማኅበር አባል በመሆን ሥራቸውን ሊያካሂዱ ወይም የማኅበር አባል ሳይሆኑ ሥራቸውን በግላቸው ሊያካሂዱ ይችላሉ::

## ፲፫. ስለማኅበራት መቋቋም

፩/ በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማኅበር ሊያቋቁሙና አባል ሊሆኑ ይችላሉ::

፪/ በመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ውድድር መኖሩን ለማረጋገጥ በአንድ ማህበር የሚታቀፉትን የአባላት ብዛት ባለሥልጣኑ ይወስናል::

## 10. Budget

The budget of the Authority shall be drawn from the following sources:

1/ license fees and service charges collected by the Authority;

2/ governmental subsidies; and

3/ any other source.

## 11. Books of Accounts

1/ The Authority shall keep complete and accourate books of accounts.

2/ The books of accounts and other financial documents of the Authority shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

## PART THREE

## PUBLIC COMMERCIAL ROAD TRANSPORT ACTIVITIES AND PUBLIC COMMERCIAL ROAD TRANSPORT ASSOCIATIONS

## 12. Undertaking Public Commercial Road Transport Activities

1/ Any individual or an enterprise established in accordance with the law may engage in public commercial road transport.

2/ Persons and enterprises, licensed to engage in public commercial road transport, may carry out their activities either by becoming members of associations to be established in accordance with Article 13 of this Proclamation or on their own without becoming members of any association.

## 13. Establishment of Associations

1/ Persons and enterprises engaged in public commercial road transport may establish and join public commercial road transport associations.

2/ The Authority shall, in order to ensure the provision of competitive road transport services, determine the number of members that may join an association.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ማኅበር በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ የተገኘውን ማንኛውንም በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሠማራ ሰው ወይም ድርጅት በአባልነት የመቀበል ግዴታ አለበት::

፬/ በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት በአንድ ጊዜ በአንድ የሥምሪት መስመር ውስጥ ከአንድ በላይ በሆኑ ማኅበራት ውስጥ አባል ሊሆን አይችልም::

፭/ ባለሥልጣኑ የማኅበራትን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል::

## ፲፬. ተፈጻሚነት የሚኖረው ሕግ

በፍትሐ ብሔር ሕግ ከአንቀጽ ፬፻፬-፬፻፹፪ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማኅበሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤ ሆኖም በነዚሁ ድንጋጌዎች ለፍትሕ ሚኒስቴርና ለማኅበሮች ጽሕፈት ቤት የተሰጠው ኃላፊነት ማኅበራቱን በሚመለከት በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ ተላልፎአል::

## ፲፭. ስለማኅበራት ምዝገባ

፩/ ማናቸውም ማኅበር እንደተቋቋመ ወዲያውኑ የምዝገባ ማመልከቻውን ከማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ጋር አያይዞ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት::

፪/ ለባለሥልጣኑ የምዝገባ ማመልከቻ ሲቀርብለት፤

ሀ) የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ሕግንና ባለሥልጣኑ ያወጣውን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ የተከተለ መሆኑን፣

ለ) አግባብነት ያለው ማንኛቸውም ሕግ የሚጠይቀው ሁኔታ መሟላቱን በማረጋገጥ፣ እና

የተወሰነውን የመመዝገቢያ ክፍያ በማስከፈል ማኅበሩን ይመዘግበዋል::

፫/ ባለሥልጣኑ የማኅበሩን የመመዝገቢያ ጥያቄ የማይቀበለው ከሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለጽ በ፯ ቀናት ውስጥ ለማኅበሩ ማስታወቅ አለበት:: ባለሥልጣኑ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በማመልከቻው ላይ አንዳችም ውሳኔ ካልሰጠ ማኅበሩ እንደተመዘገበ ይቆጠራል::



3/ Subject to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, any association shall be obliged to accept the membership of any person or enterprise engaged in public commercial road transport provided that such person or enterprise satisfies the requirements of membership as provided for in the statutes of the association.

4/ No person or enterprise engaged in public commercial road transport shall belong, within the same route of operation, to more than one association at a time.

5/ The Authority shall issue model statutes of associations.

## 14. Applicable Laws

The provisions of Article 404-482 of the Civil Code shall, in so far as they are not inconsistent with the provisions of this Proclamation, apply to public commercial road transport associations; provided, however, that all responsibilities assigned to the Ministry of Justice and the Office of Associations by said provisions are, with respect to such associations, hereby transferred to the Authority.

## 15. Registration of Associations

1/ Every association shall, promptly upon its establishment, submit to the Authority an application of registration together with its statutes.

2/ When an application of registration is submitted to it, the Authority shall, upon ascertaining that:

a) the statutes are consistent with the law and model statutes issued by it; and

b) other requirements of any applicable law are fulfilled;

and upon the payment of the prescribed fee, register the association.

3/ If the Authority refuses to register the association, it shall, within 7 days so notify the association giving reasons therefore. If the Authority fails to take any action with respect to the application for registrations within the specified time, said association shall be deemed registered.

፬/ ማኅበሩ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በሕግ የሰውነት መብት ያገኛል።

**፲፮. የምዝገባ ዕድሳት**

፩/ ማንኛውም ማህበር በየዓመቱ ከመስከረም ፩ ቀን እስከ የካቲት ፴ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈፀም ምዝገባውን ማሳደስ አለበት።

፪/ ምዝገባው በየዓመቱ ካልታደሰ ማህበሩ ሥራውን አይቀጥልም።

**፲፯. የማኅበራት ዓላማና ተግባር**

ማኅበራት የሚከተሉት ዓላማዎችና ተግባሮች ይኖራቸዋል፣

፩/ ለአባላት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የስምሪት ፕሮግራም ማዘጋጀትና እንደ አግባቡ በባለሥልጣኑ ሲጸድቅ ማስፈጸም፣

፪/ ለአባላት የጋራ ጥቅም የሚያገለግሉትን የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መናኸሪያዎችን፣ የመንገድ ጣቢያዎችን፣ የጭነት ማከፋፈያ ጽ/ቤቶችን፣ የጥገና ተቋሞችን፣ የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎችን፣ የመለዋወጫ ዕቃ መደብሮችንና የመሳሰሉትን ማቋቋምና ማካሄድ፣

፫/ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ሰነዶችን በሚገባ መያዝና በባለሥልጣኑ ሲጠየቁም ማቅረብ፣

፬/ ስለመንገድ ትራንስፖርት የወጡትን ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አባላት እንዲያውቁና እንዲያከብሩ ማድረግ፣

፭/ የአባላቱ ተሽከርካሪዎች የሚያደርሱትን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የሚያስችል የግንዛቤ ማዳበሪያና ስልጠና ስርዓት ማመቻቸት፣ እና

፮/ ከሥራቸው ጋር በተገናኙ ሌሎች ሕጋዊ ተግባሮችን ማከናወን።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፰. የመረጃ ማዕከል ስለማቋቋም**

፩/ ባለሥልጣኑ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለማሰባሰብና ለማጠናቀር የመረጃ ማዕከል ያቋቁማል።

4/ The association shall attain legal personality as of the date of its registration.

**16. Renewal of Registration**

1/ An association shall renew its registration upon payment of the appropriate fee within the period of *Meskerem* 1 upto *Yekatite* 30 every year.

2/ The association shall cease operating where it has not renewed the permit annually.

**17. Purpose and Duties of Associations**

Associations shall have the following purposes and duties:

1/ to prepare trip schedules for public service vehicles of their members; and enforce same upon approval by the Authority, as the case may be;

2/ to establish and operate common facilities such as public service vehicles' terminals, road stations, freight distribution offices, repair centers, fuel depots, spare parts shops and the like;

3/ to properly keep necessary information and documents in accordance with directives to be issued by the Authority; and submit same to the Authority when requested;

4/ to promote, among their members, the awareness and observance of laws, regulations and directives relating to road transport;

5/ to promote awareness and facilitate training system with a view to minimizing traffc accidents caused by vehicles of their members; and

6/ to perform other lawful activities relating to their duties.

## PART FOUR
## MISCLLANEOUS PROVISIONS

**18. Establishment of Data Center**

1/ The Authority shall establish a data center to collect and compile the necessary information in relation to transport.

፪/ የክልል ቢሮዎች፣ የፌደራልና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች፣ የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማህበራት፣ ግለሰቦች እና ሌሎች ድርጅቶች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከትራንስፖርት ጋር የተያያዘ አስፈላጊውን መረጃ በወቅቱ ማቅረብ ወይም ማስተላለፍ አለባቸው::

፫/ አስፈላጊውን መረጃ ለማስተላለፍ የሚረዳ የናሙና ቅጽ ባለሥልጣኑ ያዘጋጃል::

## ፲፱. በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎችና ድርጅቶች ግዴታ

በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎችና ድርጅቶች ስለመንገድ ትራንስፖርት የወጡትን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ማክበር አለባቸው::

## ፳. ስለብቸኛ መብቶችና ውሎች

፩/ ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዓለም አቀፍና በአገር አቋራጭ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለተሠማሩ ሰዎች፣ ድርጅቶች ወይም ማህበራት የተረጋገጠ ገቢ የሚያገኙበትን ሁኔታ በመፍጠር የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት በማያገኙ ወይም በቂ ባልሆነባቸው መስመሮች እንዲሰሩ ለማበረታታት ብቸኛ ወይም የተወሰኑ መብቶች ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ ያወጣል::

፪/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ማንኛውም አስጫኝ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ጋር ብቸኛ የማጓጓዣ ውል የማድረግ መብቱን የማገድ ወይም የመገደብ ውጤት አይኖራቸውም::

## ፳፩.ተሽከርካሪዎችን የማስመዝገብ ግዴታ

፩/ የፍጥነት ወሰኑ በሰዓት ከ፳ ኪሎ ሜትር ከማይበልጥ ልዩ ተንቀሣቃሽ መሳሪያ በስተቀር፣

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት ያልተመዘገበ፣ እና

ለ) ተገቢውን የመኪና ሰሌዳ ወይም ሌላ የመለያ ምልክት የሌለውን፣ተሽከርካሪ በማናቸውም መንገድ ላይ መንዳት ክልክል ነው::

፪/ ተገቢው የመኪና ሠሌዳ ወይም ሌል የመለያ ምልክት አለመኖር ተሽከርካሪውን እንዳልተመ ዘገበ ስለሚያስቆጥረው ተገቢው ምርመራ እስኪ ፈጸም ድረስ ፖሊሲ እንዲህ ያለውን ተሽከርካሪ ይዞ ለማቆየት ይችላል::

2/ The State Bureaux, Federal and State Police Commissions, public commercial road transport associations, individuals and other organizations shall submit or transfer the necessary information in relation to transport as per the directives to be issued by the Authority.

3/ The Authority shall issue model format that assists to transfer the necessary information.

## 19. Obligations of Persons and Enterprises Engaged in Public Commercial Road Transport

Persons and enterprises engaged in public commercial road transport shall observe laws, regulations and directives issued relating to road transport.

## 20. Exclusive Rights and Contracts

1/ The Authority may, where it finds it necessary, issue directives that enable the granting of exclusive or restricted franchises to persons, associations or organizations engaged in cross-country and international commercial road transport within a view to encouraging investors to engage in the provision of public commercial road transport to localities where there is no such service or where it is inadequate.

2/ Nothing herein contained shall be deemed to prohibit or restrict the right of any shipper to conclude exclusive contracts of carriage with any person or enterprise engaged in public commercial road transport.

## 21. Duty to have Vehicles Registered

1/ No vehicle, except special mobile equipment with a maximum speed of less than 20 k.m per hour, shall be driven or operated on any road unless said vehicle:

a) has been registered in accordance with regulations and directives issued hereunder; and

b) bears the appropriate plates or other identification marks.

2/ The absence of the appropriate registration plates or other identification marks shall constitute *prima facie* evidence that the vehicle has not been registered and the police may detain said vehicle pending the making of appropriate inquiries.

**፳፪. <u>የመንጃ ፈቃድ አስፈላጊነት</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው ዓይነቱ ተለይቶ የተገለጸን ባለሞተር ተሽከርካሪ ለመንዳት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የተሰጠው የጸና የመንጃ ፈቃድ ከሌለው በስተቀር በማናቸውም መንገድ ላይ ማናቸውንም ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት አይችልም፡፡

፪/ ማናቸውም የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የጸና የመንጃ ፈቃድ የሌለው ሰው ተሽከርካሪውን እንዲነዳ መፍቀድ የለበትም፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌ ቢኖርም፣ የመንጃ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች የባለሞተር ተሽከርካሪ አነዳድ ለመማር መንዳት የሚችሉበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፳፫. <u>የባህረኛና የባቡር ነጅነት ፈቃዶች</u>**

፩/ ማናቸውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፍቃድ ካላገኘ በስተቀር ባህረኛ መሆን ወይም በኢትዮጵያ ሀዲዶች ላይ ባቡርን ማሽከርከር አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ከዚህ አዋጅ መጽናት በፊት በሚመለከተው አካል የተሰጠ ፈቃድ በፈቃዱ እስከተመለከተው ጊዜ የጸና ይሆናል፡፡

**፳፬. <u>ስለሥልጣን ውክልና</u>**

፩/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል እንደ አግባቡ ለክልል ቢሮዎች፣ ለማዘጋጃ ቤቶችና ለሌሎች መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ላልሆኑ አካላት በውክልና መስጠት ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ውክልና የተሰጣቸው አካላት በውክልና የተቀበሉትን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ሲያውሉ ስለትራንስፖርት የወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና በባለሥልጣኑ የሚወጡ ደረጃ ዎችን መከተልና መጠበቅ ይገባቸዋል፡፡

**፳፭. <u>የተሻሩና ጸንተው የሚቆዩ ሕጎች</u>**

፩/ የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፺፪ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡



**22. Requirement of Holding a Driving License**

1/ No person may drive a motor vehicle on any road unless he is a holder of a valid driving license, issued in accordance with regulations and directives issued hereunder, authorizing him to drive the particular type of motor vehicle.

2/ No owner of any motor vehicle may permit any person to drive his vehicle unless the person is the holder of a valid driving license.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) and (2) of this Article, conditions under which persons not holding valid driving licences may drive for learning shall be determined by directives to be issued by the Authority.

**23. Requirement of Permit for Seafarers and Train Operators**

1/ No person shall be engaged as seafarer or operate a train on Ethiopian rail ways unless he has obtained a permit granted by the Authority.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article any permit granted by the concerned organs prior to the coming into force of this Proclamation shall remain valid until such time as indicated in the permit.

**24. Delegation of Powers**

1/ The Authority may, where necessary and as may be appropriate, delegate part of its powers and duties to State Bureaux, municipalities and other government or non-government organs.

2/ The organs referred to in Sub-Article (1) of this Article, shall in exercising the powers and duties delegated to them, follow and observe proclamations, regulations, directives and standards relating to transport set by the Authority.

**25. Repeal and Savings**

1/ The Road Transport Regulation Proclamation, No. 14/1992 is hreby repealed.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በአዋጅ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፹፬ ወጥተው ወይም ጸንተው የነበሩ ደንቦች ሁሉ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደወጡ ተቆጠረው የፀኑ ይሆናሉ::

፫/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

## ፳፮. ስለመብትና ግዴታዎች መተላለፍ

፩/ በአዋጅ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፹፬ ተቋቁሞ የነበረው የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል::

፪/ የአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ባለሥልጣንና የድሬዳዋ ከተማ የትራንስፖርት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል፤ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሆነውም ይደራጃሉ::

## ፳፯. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩/ በአዋጅ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፹፬ መሠረት የተቋቋሙ ማህበራት በዚህ አዋጅ እንደተቋቋሙ ተቆጥረው ሥራቸውን ይቀጥላሉ::

፪/ ክልሎች የራሳቸውን ህግ እስኪያወጡ ድረስ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ትራንስፖርት ነክ በሆኑት ጉዳዮች ላይ በክልሎች ውስጥ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል::

## ፳፰. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ይህን አዋጅ በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል::

## ፳፱. ቅጣት

ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል::



2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, all regulations issued under or validated by Proclamation No, 14/1992 shall, in so far as they are not inconsistent with the provisions of this Proclamation, be deemed to have been inssued under this Proclamation and shall continue in force.

3/ Any other proclamation, regulations, directives or practice inconsistent with the provisions of this Proclamation shall have no effect on matters stated hereunder.

## 26. Transfer of Rights and Obligations

1/ The rights and obligations of the Road Transport Authority established under Proclamation 14/1992 are hereby transferred to the Authority.

2/ The rights and obligations of the Addis Ababa City Transport Authority and the Dire Dawa Transport Agency are hereby transferred to the Authority, and they shall be organized as branch offices of the Authrotiy.

## 27. Transitory Provisions

1/ Associations established pursuant to Proclamation No. 14/1992 shall be considered as being established by this Proclamation and shall continue their activities.

2/ Until the States issue their own law the privisions of this Proclamation shall apply to the States in the affairs related to transport,

## 28. Power to Issue Regulations

The Council of Ministers may issue Regulations for the proper implementation of this Proclamation.

## 29. Penality

Any person who violates the provisions of this Proclamation and Regulations issued hereunder shall be punishable in accordance with the Penal Code.

**፴. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከሐምሌ ፴ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፴ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**30. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the 6th day of August, 2005.

**Done at Addis Ababa, the 6th day of August, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**